# <u>በዜሮ ማጣፋት</u>

የትግሬ ሀርነት ፤ ዘርኗቸው የበቀሉ
አገር ያፈረሱ ፤ አገር የበደሉ
በግል ጥላቻ ፤ እርስበርስ ቢጣሉ
ዛሬም ከጎጣቸው ፤ መቼ ፎቀቅ አሉ
የኢትዮጵያ ደጀን ፤ አልተባለ ቃሉ
ስልቻን ቀልቀሎ ፤ አረና ተባሉ
ጎሳ እያመለኩ ፤ አልሸሹም ዞር አሉ
ዳቦውን ይልሳል ፤ ሌባ ሰው ላመሉ ።

አገር የበተነ ፤ አገር የቆረሰ
በደም የታጠበ ፤ ደምን ያፈሰሰ
ከግር እስከ አናቱ ፤ በወንጀል የራሰ
የዘር ልክፍት ይዞት ፤ አንዴ የረከሰ
ደደቢት ተጠምቆ ፤ በጎጥ የቀሰሰ
አላየን አልሰማን ፤ ሲባል አፈረሰ !
መች ይፈራል ዝናብ ፤ አንዴ የበሰበሰ
ይቅርታም ያባት ነው ፤ ትቢታቸው ባሰ ።

ወንጀለኛን ሸሮ ፤ ወንጀለኛን ማምጣት
ወንጀለኛን ሾሞ ፤ የወንጀል ህግ ማውጣት
ወንጀለኛን ከሶ ፤ ባወጣው ህግ መቅጣት
ደደቢቷን ፈትቶ ፤ ደደቢቷን ማግባት
በዜሮ እያባዙ ፤ በዜሮ ማጣፋት
እያደናቆሩ ፤ ሰው ግራ ማግባት
ስልጡን ፖለቲካ ፤ አይ ህሊና ማጣት
ያጃጅሉን ጀምር ፤ ለድጋሚ ቅጣት ።

ታዛቢው ... April 26, 2010